# እናንተየ! እናተስ አንደ እኔ ገርሟችሁ ይሆን?

**ጌታቸው ረዳ (ኢትዮፕያን ሰማይ አዘጋጅ) getachre@aol.com**

ለብዙ አመት የተቃዋሚ ሚዲያዎችም ሆኑ፤ ገለልተኛ የሚባሉት የአሜሪካን ድምፅ፤ጀርመን እና የመሳሰሉ ከወያኔ የተገነጠለው ቡድን ለምሳሌ ስዬ፤ገብሩ፤ወዘተ..ወዘተ.. የመሳሰሉ ከፍተኛ የህወሓት መሪዎች ለቃለ መጠይቅ ሲቀርቡ፤ የሚጠየቁት ጥያቄዎች ከአስር አመት በፊትም፤ ከሁለት አመት በፊትም፤ ትናንትም ዛሬም አሁንም ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ወይንም አብዛኛዎቹ በሕዝብ የሚታወቁ ጉዳዮችን ነው ሲጠይቋቸው የምንሰማው። "ለምን ተለያችሁ?" "አረና ምን ማለት ነው?" ወዘተ..ወዘተ.. የሚለው ጥያቄ እየተደጋገሙ ሲጠየቁ፤ በሕሊናዬ የሚመጣ ጥያቄ "እነዚህ ጋዜጠኞች የሚጠየቁ ጥያቄዎች እያጡ ነው ወይስ በትግራይ ውስጥ የተፈጸሙ በርከት ያሉ ጉዳዮችን አያውቁም ስለሆኑ ነው? የሚል ሁሌም በአግራሞት እራሴን እጠይቃለሁ።

የትግርኛው  ቪኦኤም ሆነ የአማርኛው ክፍል ወይንም የመሳሰሉት ሚዲያዎች እነዚህ ሰዎች እየደጋገሙ ሲያቀርቧቸው የምናደምጠው ነገር ስለጻፏቸው መጽሐፍት፤ወይንም ስለ አረና ፓርቲ.. ወዘተ ወይንም አስልቺ ድግምግሞሽን ነው የሚያስደምጡን። ሌላ ቀርቶ የአማርኛው ቪኦኤ የተጠቀሱት መሪዎች ጫካ ውስጥ እያሉ ተፈጸሙ ተብሎ በገብረመድህን አርአያ የተነገረው ጠንከር ያለ በተሓህት መሪዎች ላይ ያነጣጠረ ክስ፤ ለምሳሌ በድርቁ ወቅት የተፈጸመው በሚሊዮን የሚቆጠር የገንዘብ በድርቅ ለተጐዱት ሰዎች ሳይሆን የዋለው፤ አብዛኛው ለድርጅቱ "ማሌሊት (ለትግራይ ማርክሲስት ሌሊኒስት ሊግ) ማቋቋሚያ ፌስታ/ድግስ እና ለመሳሪያ ግዢ ፍጆታ፤እንዲሁም በገብረመድህን አርአያ ክስ የተጠቀሱ ጥቂት የአመራር አባላት እና የምስጢር ታማኞቻቸው የተዘረፈ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መባከኑ ተነግሮናል። ሌላ ቀርቶ ለነ ገብሩ አስራት እና የመሳሰሉ የወያኔ መሪዎች ለጤናቸው መታከሚያ እንግሊዝ አገር እና የመሳሰሉ ከፍተኛ ወጪ የጠየቀ ገንዘብ እየተከፈለላቸው እንዲታከሙ የተደረገ መሆኑንም መረጃዎች ይጠቁማሉ። ገብሩ አስራት ሁለት ጊዜ እንግሊዝ አገር ተልኮ ሕክምና እንደተደረገለት እና በጣም በሺዎች የጠየቀ የልብ ሕክምና እንደተደረገለት ገብረመድህን ነግሮናል። ገንዘቡ ደግሞ ከደርቅ የተገኘ መሆኑን የታወቀ ነው።

እንዲሁም ለሕዝቡ ከማከፋፈል ይልቅ በጥሬ ገንዘብ ለመሸጥ ሲባል እህሉን በርከታ ጉድጓዶች ውስጥ ተቀብሮ በመቆየቱ "ጠረኑ ለውጦ በስብሶ ስለገማ" ተላላለፊ በሽታ ከማስተላለፉ በፊት እንዲቃጠል የተደረገው እህል እና በሰበቡ ብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ እህል አጥቶ የትም እየተንከራተተ በበሽታ እና በረሃብ ሞቷል፡ ስለተባለው የገብረመደህን ክስ ለማረጋገጥ ያቀርቧቸው ሰዎች (አምና/ካች አምና ?) "አረጋዊ በርሔ እና ረጋሽ አዳነ ናቸው"። ከሳሹ ገብረመድህን አያወቁትም መሰለኝ "ዋናውን ባለጉዳይ/ከሳሹን ትተው አመራሩን/ተከሳሾቹን እርስ በርሳቸው ብቻ አንድናደምጣቸው አቀረቡልን (አያስቃችሁም!?)

ስየ፤ ገብሩ፤ስብሓት፤አረጋሽ፤ወዘተ. ወዘተ...በተደጋጋሚ ሲያቀርቧቸው፤ አንድም ቀን ገብረመድህን አርአያ በሰም ጠቅሶ የከሰሳቸው ሰዎች በቪኦኤ ጠርተው ከገብረመድህን ጋር አለወያይዋቸውም? ለምን? ያውም ኢሳት የሚባለው የግንቦት 7 ተ/ቪዥን ጣቢያ እማ ገብረመድህን በጣም ቅርባቸው መሆኑን እያወቁ ስብሓት ነጋን እና መሰሎች በእንግዳነት ሲያቀርቡ በነዚህ ሰዎች ላይ ገብረመደህን የሚጠቅሳቸው ክሶች እና ከባድ ጉዳዮች ፊት ለፊት አገናኝተው እንዲነጋገሩ አያደርጉም። እሱን የሚያቀርቡት ብቻውን ለማስለፍለፍ ሲሻቸው ብቻ ነው።

ይኼ ብቻ እንዳይመስላችሁ። የሐውዜኑ ጉዳይ አትርሱ። አንድም ቀን የወያኔ መሪዎች ተደጋግመው በነዚህ ሚዲያዎችም ሆኑ ባልተጠቀሱ ሚዲያዎች ሲቀርቡ ገብረመድህን አርአያ ጠርተው ፊት ለፊት አገናኝተው ለጥያቄ አቅርበው "ህወሓት አስፈጸመው የተባለው የሐውዜኑ ጭፍጨፋ" አላስደመጡንም።

አልጨረስኩም! ምን ይህ ብቻ። ገብረመደህን አርአያ በግል ደብዳቤ ልኰልኝ በመጽሐፌ (የወያኔ ገበና ማሕደር ውስጥ ) የተጠቀሰ የአጽረጋ እና የመሳሰሉ "ውስተ - መሬት" (አንደር-ግራውንድ) በሺዎቹ የሚቆጠሩ አማራዎች የእስርቤቱ ህንጻ (አንድር-ግራውንድ) ቆፍረው ካጠናቀቁ በኋላ፤ በቆፈሩት ጉድጓድ ውስጥ ለመቃብር ከታቀዱት ባንዳንድ ጉድጓዶች ውስጥ ተረሽነው በጅምላ መቀበራቸው በላከልኝ ደብዳቤ (በመጽሐፌ የተካተተውን ይመልከቱ) ያወሳል። ይህ ጉዳይ እሱ ብቻ ሳይሆን ታጋዮች የነበሩም እንደተፈጸመ ነግረውኛል። ይህ እና የመሳሰሉ በርከት ያሉ ምስጢሮች ለሕዘቡ ለማሳወቅ ገብረመድህን እና

የህወሓት መሪዎችን ፊት ለፊት ለማነጋጋር የማይፈቅዱት ምን ይሆን? ገብሩ አሁንም አሜሪካ ውስ አለ። ለምን ከገብረመድህን ጋር አያነጋግሩትም?

ወያኔ እና ኤርትራኖች ካርቱም ውስጥ በአሜሪካን ባለስልጣኖች እና ሲአይኤ በላካቻው አሜሪካኖች ደርግን ለመጣል ሲባል “ካርቱም” ውስጥ የተደረገው ምስጢራዊ ጉባኤ እና የተደረገላቸው የስለላ እገዛ ምስጢር ለምን አይነግሩንም? ወያኔዎች ባይነግሩንም ‘ኤርትራኖች ነግረውናል። ሌላ ቀርቶ በኤርትራኖች ተይዘው የነበሩ የተለያዩ ሲቪሎች እና ጸረ ኤርትራ ትግል ነበራችሁ የተባሉ ኢትዮጵያዊያን እና ኤርትራዊያኖች ከነበሩበት ከአስመራ እስር ቤት ታፍሰው ኮንጎ ድረስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ታጭቀው ለአልማዝ ቁፈራ በኤርትራኖች መሪነት በካቢላ ተቀባይነት “አልማዝ እና ወርቅ” ቁፋሮ ከገቡ በኋላ፤ ምስጢሩ እንዳይታወቅ በማለት እዛው የተረሸኑ መሆናቸው “ኤርትራኖች” ነግረውናል። ወያኔዎች አፋቸው ለምን ከደኑ? ይህ እና የመሳሰሉ ምስጢሮች ደግሞ በራሴው ብሎግ ከ4 አመታት በፊት ተጽፎ ነበር። ጋዜጠኞቹ ይህን ምስር አያውቁም ሆነው ነው ወያኔዎችን ለመጠየቅ ያልደፈሩት?

ሚዲያዎቹ የተጠቀሱት የወያኔ መሮችን የሚጠዩቋቸው፤ የተዘረዘሩት ከባድ ጉዳዮች ከመጠየቅ ይልቅ “የማስታወቂያ ደላሎች ይመስል” ስለ አዲስ መጽሐፋቸው ሽያጭ ወዘተ ወዘተ ወንም “ከአቶ መለስ ጋር ምን አጣላችሁ?” የሚለው የሰለቸ ጥያቄ ነው ዘወትር ሲጠይቋቸው የምናደምጣቸው። የጠቀስኳቸው ሚዲያዎች፤ ኢሳትም ጭምር “በተለይ” ቪ ኦ ኤ “አርካይቫቸው/የአውዲው ፋይል አሰፋፈር” ግራ ስለሚያጋባኝ “ፍሊጋው/ቀኑ አመተምህረቱ” መለየት ስላስቸገረኝ እና ስለሰለቸኝ፤ ማድመጥ ትቼአቸው አለሁ። ባደምጣቸውም በሁለት ወር አንዴ ስለሆነ፤ የጠቀስኩዋቸው አበይት ጉዳዮች የተገለጹ ከሆነ አላውቅም። እኔ እስከማውቀው ድረስ ግን እነዚህ ሚዲያዎች የተጠቀሱ አበይት ጉዳዮች “ከሳሹ እና ተከሳሾቹ” ፊት ለፊት አምጥተው ለሕዝብ ከማስደመጥ ይልቅ “ወደ መጽሐፍት አሻሻጭነት ሥራ የተገቡ ይመስላሉ። ለምን?

በነገራችን ላይ የገብሩ አስራትን አዲስ መጽሐፍ ወዳጄ ሰጥቶኝ ዛሬ ነው ወደ እጄ የገባው። የህወሓት አመሰራረት በሚለውም ሆነ በኢሕአፓ ጉዳይ የተነተነው መጀመሪያው አካባቢ ላይ ‘ገረፍ ገረፍ’ አድርጌ ባየው፤ በሁለቱ ምዕራፎች ወያኔዎች የነበራቸው፤ የጻፉት፤ ለሕዝብ ይፋ ያደረጉት፤ የቋጠሩት ስለ “አማራ ጥላቻ” ወይንም ጉዳይ አንዲትም ቃል አልጠቀሰም። መጽሐፉን እስካነበው ድረስ መቆጠብ አለብኝ እንጂ መጠቀስ በነበረበት ምዕራፍ ካልተጠቀሰ የት እንደሚጠቀስ መገመት አልቻልኩም። ለማንኛውም መጽሐፉ ወደ 500 ገጽ ያካተተ ስለሆነ ትችቴን መጽሐፉን እስክጨርስ ላቆየው እንጂ ከጅምሩ ከዋናው ብልቱ ካልተጠቀሰ፤ በየትኛው ገጽ እንደሚጠቀስ መገመት አስቸግሮኛል። ገብሩ በዚህ ሰንክሳር ምጽሐፍ ውስጥ ስለ አማራ እና ወያኔዎች ካልጠቀሰ በትችቴ ላይ እንዴት እንምጮኽበት አለውቅም።

በነገራችን ላይ ገዛ ተጋሩ በሚባለው “ጸረ አማራ” የወያኔዎች ፓል ቶክ ክፍል ውስጥ ባለፈው ሰሞን በአመርኛ የሰጠው ቃለ መጠይቅ ውስጥ “እስከ መገንጠል ሚለው አንቀጽ 39 ጭራሽ በሚመጣው ሕገ መንግስት መካተት የለበትም ማለቱ አስደስቶኛል። ካሁን በፊት ቪ ኦ ኤ ቀርቦ በሕዳር 11/2007 አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር አንቀጽ 39 እሱ በሚመራው በዓረና ድርጅት ውስጥ መካተቱን ገልጾ እንደነበር ይታወሳል። ከዚያም በዚያ ጠንካራ አቋም ነበረው። አሁን በሰጠው ቃለ መጠይቅ ግን በማንኛወም ሕገመንግስት መካተት እንደሌለበት አገር አድን ሳይሆን፤ ኣገር አፍራሽ እና ኮሚኒስታዊ እንደሆነ መግለጹ ደስ ብሎኛል። በተረፈ መጽሐፉን አንብቤ እስከጨርስ ድረስ ከመተቸት ተቆጥቤአለሁ።

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ ብሎግ አዘጋጅ) getachre@aol.com (Editor Ethiopian Semay)